ጤና ይስጥልኝ፤ በዚህ የዕዝራ ስርጭት

## የሕዝብ ሰው

የሕዝብ ሰው በሚል ስለ መንጋ ብቻ አስደሳች መሪዎች ባህርያት በማጥናት ሁለት መሪዎችን ተመልከተን ነበር። በዚህ የመጨረሻውን ሰው እናያለን። ጲላጦስ ሕዝብ ሊያስደስት ብሎ እውነትን የሰቀለ ሰው ነው። ያኔ ክርስቶስ እንደተሰቀለ ዛሬም መንጋን ለማስደሰት ሲባል፥ ጎራን ላለማስቀየም ሲባል እውነት ይሰቀላል፤ ቃሉ ይሸፈናል፤ ጌታ ይወገዳል። በስፍራው ወንበዴው በነጻ እንደተለቀቀ የሚያወናብድ ትምህርት ይነሰነሳል። ያሳዝናል።

## ብሮር ወይም ብሞት

በሁለተኛው የጳውሎስን የፊልጵስዩስ መልእክት ቀጥለን እናጠናለን። ብኖር ወይም ብሞት አለ ጳውሎስ። ክርስቲያኖች የምንኖርለት ብቻ ሳይሆን የምንሞትለትም ምክንያት ያለን ሰዎች ልንሆን ተጠርተናል። ለምንኖርለት ዓላማ ለመሞት ካልቆረጥን ልንኖርለት አንችልም። ይህ እውነት ነው። ለምን ቢባል ቁርጠኞች ካልሆንን እምነታችን የተግባር ሳይሆን የአፍ ብቻ ነው ማለት ነዋ! ለምንኖርለት ነገር ልንሞት ከተጠየቅን አንሞትማ! እንሸሻለና! ስለዚህ መኖራችን የለበጣ ነው። ለምንኖርለት የምንሞትለት ከሆንን ቁርጠኞች ነን። ቁርጠኞች ከሆንን መኖራችንም ሙሉ ደስታ ነው። ኑሮ ለጌታና ከጌታ ጋር ፍጹም ሐሴት ነው። ጳውሎስ ለሞተለት ጌታ የኖረ፥ ለኖረለት ምስክርነት የሞተ ሰው ነው።

## የኢዮስ 'ፈዋሽ'

እግዚአብሔር ፈዋሽ አምላክ ነው፤ ይህን እናምናለን። ነገር ግን የፈውስ 'አገልጋዮች' የሚባሉ ሰዎች በሽተኞች ሳይፈወሱ እንደተፈወሱ ሲናገሩ ታዝባችሁ ታውቃላችሁ? ሕመማንስ ሳይፈወሱ እንደተፈወሱ እንዲመሰክሩ ሲነሣሱና ሲጋበዙ ወይም በራሳቸው ተነሣሽነት እንደዳኑ ሲመሰክሩ ሰምተን እናውቃለን? ፈውሰኞች ያልተፈወሱ ሰዎችን እንደተፈወሱ ሲያውጁ እነዚህ ሰዎች መሳሳታቸውንና ማጥፋታቸውን ቢጠየቁና ይህ ቢጋለጥ ነውር ነው? ያልተፈወሱ ሰዎችስ አለመፈወሳቸውን መካዳቸው ራሳቸውን የሚጎዳ ክህደትና ሌሎችን የሚያስት ስሕተት ብቻ ሳይሆን ውሸትና ኃጢአት መሆኑን አስተውለናል? በተለይ ፈውሱ የሌለና እንደሚዘገን ያለ ጉም ብቻ ሳይሆን አደገኛ ሲሆን ምን እናደርጋለን? ይህ መጣጥፍ አዲስ ሳይሆን ከዚህ ቀደም ከታተመ መጽሐፌ የተወሰደ ነው።

መልካም ንባብ።

ዕዝራ ስነ ጽሑፍ፥ ዘላለም መንግሥቱ

# የሕዝብ ሰው

## የመንጋ ብቻ አስደሳች ሰው መልክ

**ክፍል ሦስት - ጲላጦስ**

**ጲላጦስም የሕዝቡን ፈቃድ ኪያደርግ ወዶ**
**በርባንን ፈታላቸው፥**
**ኢየሱስንም ገርፎ እንዲሰቀል አሳልፎ ሰጠ።**

ማር. ፲፭፥፲፭

ባለፉት ጊዜያት በጀመርነው የመንጋ አስደሳች መሪዎች ዳሰሳ ሦስት መሪዎችን እንድናይ ቃል ገብቼ ነበር። የመጀመሪያውን ምሳሌ የሚሆነንን ሰው ንጉሥ ሰሎሞንን እና ቀጥሎም ሌላውን የሕዝብ ሰው ንጉሥ ሳኦልን ተመልክተን ነበር። በዚህ በመጨረሻው ደግሞ ከአዲስ ኪዳን ጲላጦስን እንመለከታለን።

### የቤትሕ ያዘህ!

ባለፈው ነቢዩ ዕንባቆም በዘመኑ ስለነበረው የፍትሕ መጓደል እሮሮ ሲያሰማ፥ *ስለዚህ ሕግ ላልቶአል፥ ፍርድም ድል ነሥቶ ኢይወጣም ኃጢአተኛ ጻድቅን ይከብባልና ስለዚህ ፍርድ ጠማማ ሆኖ ይወጣል* አለ፤ ዕን. ፩፥4። በከተማችን የሚገኝ አንድ ወዳጃችን በደርግ ዘመን ከመንገድ ታፍሶ ከርቸሌ ወኅኒ ወረደ። ከ7 ዓመታት በኋላ ሲለቀቅ የተቀበሉት ቅጣት በቂ ሆኖ በመገኘቱ ተለቀዋል ከሚል ማስታወሻ ጋር ነበር። ባለፈው የፊልጵስዩስ ጥናት ከግለ-ታሪክ መጽሐፉ ብዙ የጠቀስኩት አገልጋይ መጋቢ ተስፋዬ ጋቢሶ አብረውት ከታሰሩት ጋር ያንኑ ያህል ጊዜ ታስረው በተለቀቁ ጊዜም ይኸው ቃል “. . . እገሌ የተባሉ አብዮቱ የማይፈልገውን አቅጣጫ ሲያስፋፉ በመገኘታቸው ከ-እስከ- በቁጥጥር ስር ከቆዩ በኋላ የታሰሩት በቂ ሆኖ እንዲፈቱ ስለተወሰነ ተለቀዋል” ተብሎ ነበር ከወኅኒ የወጡት።[1]

ዲሞክራሲ በሰፈነባት አሜሪካም ፍትሕም ፍርድም ስፍራቸውን የሚተዉበት ጊዜ አያሌ ነው። በቅርብ ሳምንታት ያነበብኩት የጆን ግሪሻም The Innocent Man የተሰኘ ኢ-ልብ ወለድ መጽሐፍ የዚህ አንድ ምስክር ነው። ይህ ታሪክ አንዲት ሴትን የመድፈርና የመግደል ወንጀል ፈጸመ ተብሎ ሞት ተፈርዶበት ቅጣቱ የሚፈጸምበትን ቀን 12 ዓመት ሙሉ እየጠበቀ ቆይቶ ከትልቅ ጉስቁልና በኋላ ንጹህ ሆኖ በመገኘቱ የተፈታ ራን ዊልያምሰን የተባለ ሰው ታሪክ ነው። ይህ ሰው ከተፈታ ከ5 ዓመታት በኋላ በፈረንጆች አቆጣጠር በ2004 ሞተ። በእስራቱ ወቅት ግን የፍርዱ አቅጣጫ እንዲለወጥ ያስገደደው ደብዳቤ ሲመጣ ሊገደል 5 ቀናት ብቻ ቀርተውት የነበረበት ጊዜም ነበረ። በኋላ ወንጀሉን የፈጸመው ሰው ተገኝቶ እድሜ ይፍታህ ተፈርዶበታል። ራን 12 ዓመታት ንጹሕ ሳለ ተቀጣ እንጂ ሞት ቢበየንበትም ቅሉ አልሞተም። ብዙ ባልፈጸሙት ወንጀል የሞቱ ሰዎች በየአገሩ አሉ።

ጥንትም በዘመናችንም ፍትሕ ቦታውን ልቅቆ ያውቃል ይለቅቃልም። አስለቃቂዎቹ ግን ምክንያታቸው ይለያያል። ብዙ ጊዜ ለራስ፥ ማለትም፥ ፍትሑን አቅመ ቢስ ለሚያደርጉት ሰዎች ጥቅም ተብሎ የሚደረግ ሲሆን ሌላው ግፊት ደግሞ በቀል ነው። የጲላጦስ ፍርድ በጥቂቱ ጥቅም ከመጠበቅ ጋር ይቆራኛል ብለን ማሰብ እንችላን። ተወዳጅ ሆኖ ለመገኘት። ለገዥው መንግሥት ጥቅም ነውም ማለት ያስችላል፤ ኢየሱስ ሌላ ተደራቢ ምድራዊ ንጉሥ ተደርጎ ከተወሰደ ማለት ነው። ግን ለጲላጦስ ሥልጣኑ ያልተደላደለ መሠረት ላይ አልነበረምና ይህን ሊፈራ የተገባው አይደለም። ፍትሕ እንዳይዛባ ቢያደርግ ቢያንስ ሮማዊው የሥልጣን ተዋረድ ይደግፈው ነበር እንጂ አይኮንነውም። ጎሊናውን ለራሱ ትተን ማለት ነው።

### የመስቀሉ መንገድ

ጌታ ለፍርድ በቀረበበት ዘመን ጲላጦስ የይሁዳ ገዥ ነው። ይሁዳ ከአራቱ በሉቃ. 3፥1 የአራተኛው ክፍል የተባለው) የዚያ ግዛት የሮም ክፍለ አገሮች አንዷ ናት። ገዥው የሮም ዋና ወኪል ወይም እንደራሴ ገዥ ነው። ሮማዊ ዜጋ ሆኖ ወደ ቄሣር ይግባኝ ካላለ የገዥው ፍርድ የመጨረሻው ነው።

የምንመለከተው ሰው ጲላጦስና ሕዝባዊነቱ ቢሆንም የጌታን ፍርድ ፈራጁ፥ ዘላለማዊውን ኪዳን አታሚው ወይም ቀዳጁ አድርገን እንዳንወስደው እፈልጋለሁ። ጲላጦስ በመስቀሉ ታሪክ ውስጥ አንድ መሣሪያና ተዋናይ እንጂ ሌላ አይደለም። ዋናው ባለ ታሪክ ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። ገድሉም መስቀሉ ነው። ቀድሞም የመጣው ለዚያ ጊዜ ነው፤ በመስቀል መሞቱና ኃጢአታችንን መሸከሙ ከዓለም መሠረት ጀምሮ እቅድ የተያዘለት ነው (ራእ፣ 13፥8) እንጂ ከመቶዎች ዓመታት በፊት በነቢያት የተነገረ ብቻ አይደለም። ነፍሱን ሊያኖራት፥ ሊያነሣትም ሥልጣን ያለው እርሱ ራሱን ወድዶ ነው ስለ ኃጢአታችን አሳልፎ የሰጠው። ስለ ኢየሱስ ስናስብ ፍትሕ ተጓድሎበት በስሕተት እንደተገደለ ከቶም ማሰብ የለብንም። ይህ ዘላለማዊ መለኮታዊ ንድፍ ግን ጲላጦስን የሳተ መሪ ከመሆን ነፃ አያደርገውም።

ጌታ ወደ ጲላጦስ ከመቅረቡ በፊት የአይሁድ ሸማግሌችና የካህናት አለቆች ሊያጠፉት የተደጋገመ ሙከራ ምኞት ተመኝተዋል ሙከራም አድርገዋል። እነዚህ ያለሕግ ሊገድሉት የሞከሩባቸው ናቸው። የመጨረሻውን የተቀነባበረና የተሳካ ግድያ ትተን የቀደሙትን ለማየት እነዚህን ጥቅሶች ተመልከቱ፤ ማር. 12፥12፤ ሉቃ. 4፥29፤ ዮሐ. 5፥16-18፤ 7፥1 እና 25፤ 11፥53፤ ወዘተ።

ጲላጦስ የይሁዳ ጠቅላላ ገዥ ሆኖ በኢየሩሳሌም ፕራይቶሪዮን የሚባል የገዥው መኖሪያ ግቢ አለ እንጂ ዋና መቀመጫው የነበረው በኢየሩሳሌም ሳይሆን በቄሣርያ ነበረ። እንደ ገዢ በከልሉ ሁሉ የመገኘት ኃላፊነት አለበት። ይህ ጌታ የተሰቀለበት ጊዜ የፋሲካ በዓል ወቅት ነው። በአይሁድ ዘንድ ከታላላቅ በዓላት አንዱ ነው፤ ብዙም አይሁድና ወደ ይሁዲነት የገቡ አሕዛብ በኢየሩሳሌም የሚገኙበት ጊዜ በመሆኑ እንደ ገዥ በዚያ

[1] *በዚያን ጊዜ፥ ገጽ 103-4።*

የመገኘት ግዴታ አለበት። ጲላጦስ ስለ ኢየሱስ ጥልቅ እውቀት ያለው ሰው ባይሆንም በጊዜው ስለሆነው ነገር በቂ ግንዛቤ ያለው ሰው ነው።

## ብዙ ምስክሮችና ፍርደ-ገምድል ዳኛ

ጳላጦስ ወደ ገሹነት የመጣው ምንም የገሹነት፥ የጦር ስልት፥ የገንዘብ አስተዳደር እውቀት ሳይኖረው አይደለም። ይህ የዳኝነትና የፍትሕ እውቀትንም ይጨምራል። ከምርመራውና ከወሰዳቸው ስርዓቶች ይህንን መረዳት ይቻላል። በቂ ምስክሮችን አድምጦአል። ከራሱ ጎሊና እስከ ሚስቱ መልእክት፥ እስከ ሌላ ገሹ ምስክርነት ሰምቶአል። እነዚህን አሻፈረኝ ያላቸውን ምስክሮች እንስማ።

1. ጲላጦስ ኢየሱስን እንኳን የሚያስገድለው የሚያሳስረውም በደል እንደሌለበት አውቋል። ስለዚህ ሊለቅቀው የሚያስችለውን አማራጭ ሊጠቀም ሞከረ። ማቴ. 27፥ 17-18 እንዲህ ይላል፤ *እንግዲህ እነርሱ ተሰብስበው ሳሉ ጲላጦስ፥ በርባንን ወይስ ክርስቶስ የተባለውን ኢየሱስን ማንኛውን ልፈታላችሁ ትወዳላችሁ? አላቸው፤ በቅንዓት አሳልፈው እንደ ሰጡት ያውቅ ነበርና።* እዚህ ላይ ባለፈው እንደተመለከትነው የሕዝብ ሰው እንደ ሳኡል ይህም ሰው በውስጡ የእርስ በርስ ጦርነት የሚካሄድበት ሜዳ ይመስላል። በቅንዓት እንደሰጡት እያወቀ ግን በተቃራኒው መንገድ አልሄደም።

በሉቃ. 23፥2 *ይህ ሕዝባችንን ሲያጣምም ለቄሣርም ግብር እንዳይሰጥ ሲከለክል ደግሞም፦ እኔ ክርስቶስ ንጉሥ ነኝ ሲል አገኘነው* ብለው ይከሱት ጀመር ተብሎ ተጽፎአል። ግብር እንዳይሰጥ አልከለከለም፤ ምድራዊ ንጉሥ እንደሆነም አልተናገረም። እርግጥ ቀራጮችን ጠርቶአል እንዲከተሉት፤ ሌዊ ቀራጭ ነበረ። ዘኬዎስም የተለወጠ ሰው ሆኖአል። የኃጢአተኞችና የቀራጮች ወዳጅ ተብሎም ተጠርቶአል። ግን ይህ የመከሰሻ አቅም የለውም።

2. የጲላጦስ ልማዱና ቸርነቱ አንድ ሰው በዚህ በዓላቸው መፍታቱ ነበር። በዚህ በዓል ኢየሱስን ሊፈታ ያቀረበውን አሳብ በሁከትና ነፍሰ ገዳይነት የታሰረውን በርባንን እንዲፈታላቸው ጠየቁ። የካህናት አለቆች ሕዝቡን ያባበሉት ይህ ሰው እንዲፈታላቸው ነው። ጲላጦስ ይህ ሰው የታሰረበትን ምክንያት ያውቀዋል። በካህናቱ አሳሳቢነት ይህ ሰው እንዲፈታ መጠየቃቸው ራሱ እንቢ እንዲል ወይም የኢየሱስን ንጽህና ሊያሳየው ይችላል። ይህንንም ገፋው።

3. ከቤተ ሰቡ ውስጥ የገዛ ሚስቱ የሆነባትን አስረድታ ላከችበት። ማቴ. 27፥19 ይህን ይላል፤ *እርሱም በፍርድ ወንበር ተቀምጦ ሳለ ሚስቱ፥ ስለ እርሱ ዛሬ በሕልም እጅግ መከራ ተቀብያለሁና በዚያ ጻድቅ ሰው ምንም ሊታድርግ ብላ ላከችበት።* ምናልባት ሊያድነው ለመጣሩ ግፊት አሳድሮበት ካልሆነ በቀር ለዚህም የሰጠው ግልጥ ምላሽ የለም።

4. ጲላጦስ ኢየሱስን በመረመረበት ምርመራው የገሊላ ሰው መሆኑን ባወቀ ጊዜ የገሊላ ገዥ የነበረው ሄሮድስ በኢየሩሳሌም ነበረና ወደ እርሱ ላከው፤ ሉቃ. 23፥6-15። ሄሮድስም መርምሮ ምንም አላገኘበትምና ምንም በደል አለማግኘቱን አረጋግጦ መልሶ ላከው። በዚህ ጊዜም ንጹሕነቱን አረጋግጦ፥ *ሕዝቡን ያጣምማል ብላችሁ ይህን ሰው ወደ እኔ አመጣችሁት፤ እነሆም፥ በፊታችሁ መርምሬ ከምትከሱበት ነገር አንድ በደል ስንኳ በዚህ ሰው አላገኘሁበትም።* ሄሮድስም *ደግሞ ምንም አላገኘምና፤ ወደ እኛ መልሶታልና፤ እነሆም፥ ለሞት የሚያደርሰው ምንም አላደረገም፤ እንግዲያስ ቀጥቼ እፈታዋለሁ* አለ፤ ሉቃ. 23፥ 14-16። ቀጥቼ ሲል እንዲያውም አካላዊ ቅጣት ምናልባት ምናልባት ቢኖርበት እንጂ *ቀጥቼው* የሚለው ቃል (παιδεύσας αὐτὸν) አካላዊ ቅጣትን አያመለክትም፤ አስጠንቅቄ፥ አስተምሬ፥ አስረድቼ ማለቱ ነው። በሁለት የተቀመሙ ሮማዊ ገዦች ተመርምሮ በደል አልተገኘበትም። ንጹሕ ነው ግን ነጻ አልሆነም።

## የሕዝቡን ፈቃድ ከገዘጋይ መረ

ጲላጦስ እነዚህን ሁሉ ምስክሮች ይስማ እንጂ ኢየሱስን እንዲሰቀል አሳልፎ ሰጠው። ስለምን አሳልፎ ሰጠው? *እነርሱ ግን እንዲሰቀል በታላቅ ድምፅ አጽንተው ለመኑት።* የእነርሱ ጩኸትና የካህናት አለቆችም ቃል *በረታ።* ጲላጦስም <u>*ልመናቸው እንዲሆንላቸው*</u> *ፈረደበት።* ያንን *የለመኑትንም፥ ስለ ሁከት ሰውንም ስለ መግደል በወኅኒ ታስሮ የነበረውን* <u>*አሰፈታላቸው*</u>*፥ ኢየሱስን ግን* <u>*ለፈቃዳቸው*</u> *አሳልፎ ሰጠው።* ሉቃ. 23፥23-25።

ጲላጦስ ጌታን አሳልፎ የሰጠው ሕዝቡን ለማስደሰት ብቻ ሲል ነው። የሕዝቡ ጩኸትና የካህናት አለቆቹ ቃል በረታ። ምንም ቢበረታ ያ ጩኸትና ቃል የአንድ ጎራ ጩኸትና ቃል እንጂ የገዢ ወይም የፍትሕ ቃል አይደለም። ጲላጦስ የተሸነፈው ልመናቸው እንዲሆንላቸው፥ የተንበረከከውም ለፈቃዳቸው ነው። ከደሙ ንጹህ ነኝ ብሎ እጁን ታጠበ። ይህ የንጽሕናው ምልክታዊ ድርጊት ነው ወይስ ንጹህ ደም አሳልፎ የመስጠቱ፥ የድካሙ፥ የወንጀሉ ስስ መሸፈኛ ሻሽ ነው?

የሕዝብ ፈቃድ በጲላጦስ አገዛዝም ሲሠለጥን ይታያል። *ጲላጦስም የሕዝቡን ፈቃድ ሊያደርግ ወዶ በርባንን ፈታላቸው፥ ኢየሱስንም ገርፎ እንዲሰቀል አሳልፎ ሰጠ፤* ማር. 15፥15። ምን ሊያደርግ ወዶ? የሕዝቡን ፈቃድ ሊያደርግ ወዶ! በመጨረሻ ፍርድ ቢገመደል ወይም ከስፍራው ቢወገድ ግድ አጣ። አንድ ሰው ሞቶ አንድ ጎራ ሕዝብ ከተደሰተ ምንም አይደለም አለ። ይህ ግን አንድ ሰው ብቻ አልነበረም። ይህ የተፈረደበት ሰው እግዚአብሔር ወልድ ነው። እውነት ነው። ይህን እውነት ሊያውቅ ጥቂት ቀርቦ ነበር። ሊያውቀው እድል አግኝቶ ነበር፤ ነገር ግን *እውነት ምንድርነው?* ብሎ ጠየቀ እንጂ መልሱንም የፈለገ አይመስልም፤ ዮሐ. 18፥38።

## ዛሬም ከሕዝብ ስሜት ሲባል ንጹህነት ይሰቀላል

የሕዝብን ፈቃድ ማገልገልና ሕዝብን ለማስደሰት እግር እስኪቀጥን መቆምና መሮጥ ዛሬም ይህን ጌታና ይህን እውነት መለወጥን ያመጣል። በምዕራቡ ዓለም፥ በተለይም በዘመነኛው ዓለም ዛሬ የተለመደ ቃል ብቻ ሳይሆን ንቅናቄም የሆነ seeker-sensitive የተባለ እንቅስቃሴ ይስተዋላል። ወደ ቤተ ክርስቲያን መምጣት የሚፈልጉ ሰዎችን ስሜት ለማስደሰትና ስሜታቸውን ላለመጉዳት በመጠንቀቅ የሚደረግ አምልኮ ነው። ስለ ኃጢአት፥ ስለ ፍርድ፥ ስለ ኩነኔ፥ ስለ ዘላለማዊ ቅጣት፥ ስለ ሲዖል፥ ስለ ቅድስና፥ ፍጹም የሆነና የማይለወጥ እውነት መኖሩ፥ መስቀል፥ ወዘተ አይሰበኩም። በአጭር ቃል ወንጌል አይሰበክም። እነዚህ ነገሮች ካልተሰበኩ ምን ሊሰበክ እንደሚችል መገመት አይከብድም። ስለ ሥራ፥ ስለ ቤተሰብ፥ እንዴት ታታሪና ኑሮን አሸናፊ ስለመሆን፥ እንዴት የማያስተማምነውን ኢኮኖሚ ታግሎ ባለጠጋ እንደሚኮን ነው።

ማኅበራዊ፥ ስነ ልቡናዊና ምጣኔ ሀብታዊ ዐውደ ጥናት ነው ማለት ይቻላል።

የነዚህ ሰዎች ስብሰባ ስነ መለኮታዊው በሰብዓዊው፥ ከመለኮትና ከሰው ጋር ያለው ግንኙነት በረቂቅ ፍልስፍና የተሸፈነበት ስብሰባ ነው። አንዳንዶቹ የእሁድ መደበኛ የአምልኮ ጊዜን የማይደግፉ በሳምንት ሁለት ቀናት ምሽት የሚሰብሰቡ አንዱን ለቆዩ አድርገው ሌላውን ለነዚህ ስሜታቸውን ወድቆ እንደሚሰበር እንቁላል ለሚጠነቀቁላቸው ሰዎች የሚያደርጉ ናቸው። ለነዚህ የሚደረገው በአንድ ቴያትር ቤት ከሚደረግው ከቶም የተለየ አይመስልም። ዓላማው ወደ ቤተ ክርስቲያን ለመምጣትና ወንጌል ለመስማት ፈቃድ የሌላቸውን ሰዎች ለመድረስ የሚል ነው።

ለስሜታቸው ጥንቃቄ የሚደረግላቸው "ፈላጊዎች" መጥተው አጭርና የሚያስቅ ንግግር ሰምተው ወደ ቤታቸው ሲመለሱ ስሜታቸው ተደስቶ ሌላ ጊዜም ተመልሰው እንዲመጡ የሚጋብዛቸው አገልግሎት ነው። ዘመናዊውን የገበያ የፍላጎትና አቅርቦት ዘዬ የተከተለ አቀራረብ ነው። መሆን ያለበት ነገር ሳይሆን ያለው ኹነት ላይ ነው ትኩረት የሚደረገው። ለምሳሌ፥ ኃጢአተኛ ሰው መዳን ያለበት መሆኑ ሳይሆን ባለበት ሁኔታ እንዴት የተሻለ እንደሚሆን ነው። የሚፈልጉት ነገር በጥንቃቄ ይጠናል። በዚያ ዙሪያ በስልት የተቀረጸ ንግግርና ስነ መለኮት ይነደፋል። ያ በዘመናዊና መሥህብነት የተቀዳጀ መልክ ይቀርባል። ይህ ንቅናቄና እንቅስቃሴ ከሃያ ዓመታት ያላነሰ ጊዜ አስቆጥሮአል።

ይህን የመሰለ አዝማሚያ በዓለሙ ሁሉ እየናኘ ነው። በአገራችንም እንደ ንቅናቄ ባይታይም ሰዎች የሚያስፈልጋቸው ምንድርነው? ብሎ ያንን ብቻ አፈንፍኖ ጥቂት ሥጋንና ስሜትን የሚያስደስቱ ነገሮች ብቻ ላይ ያተኮረ ትምህርት ይዞ መከለስ ከታየ ቆይቷል። እውነት እየተገደለና መስዋእት እየተደረገ በእውነት ፈንታ ምናምንቴ ሽንገላ እየቀረበ ይታያል። እውነት በተፈጥሮው ሰዎችን የሚያስቆጣ ውስጣዊ ባህርይ አለው። እውነት ኃጢአትን ኃጢአት ይላል፤ ኃጢአተኛንም ኃጢአተኛ ይላል እንጂ፥ "ምንም አትል ደህና ነህ" አይልም። እውነትን የሚሰብክ ሰውም ማንም እንዳይቆጣና ሁሉም እንዲመጣ ሳይሆን የሰማውና የመጣው ሁሉ ከእውነት ምንጭ እንዲጠጣ የሚያቀርብ ነው።

ሕዝብን ያስቆጣል ብሎ በእውነት ላይ መቆምና እውነትን የመደበቅና የመሸፈን እርምጃ ጉዳት ብቻ ነው። የዛሬ ሁለት ዓመት ገደማ ጆኤል ኦስትን (Joel Osteen) የተባለ የዚህ መሳይ ትምህርት አስተማሪ በCNN ቴሌቪዥን ቀርቦ ሳለ ጠያቂው፥ "ታዲያ አሁን መዳን የሚገኘው በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን ብቻ ነው ትላለህን? እስላሞችስ? ሌሎች ሃይማኖተኞችስ? እንደኔ ያሉ አይሁዶችስ?" ብሎ ሲጠይቀው በሁለት ደቂቃዎች ያህል መልሱ አምስት ጊዜ ያህል ደጋግሞ፥ "እኔ እንጃ፥ እም. . . ማለቴ . . . እግዚአብሔር ነው የሚያውቀው፤ እኔ እንጃ. . . እኔ አላውቅም . . . እኔ የሰው ልብ ፈራጅ አይደለሁም" ነበር ያለው። ይህ ታዋቂና በአንዳንዶች ዘንድ እንደ ትልቅ 'ቤተ ክርስቲያን' መጋቢ የተቆጠረ ሰው ለምን እንዲህ አለ? ላለማስቆጣት! እውነት ያስቆጣል። ይህ ሰው ስለ መዳን መንገድ በግልጽ አለመናገር ብቻ ሳይሆን ሰዎችን የሚያስቆጡ የመሰለው ነገሮች ሁሉ ላይ አቋም በማጣት የሚሸሽ እና እንዲያውም በግልጽ ስሕተት የሆኑ ነገሮችን እንደ ስሕተት የማይቆጥርና የማይገልጥ ሰው ነው። ለሕዝብ ሲል፥ ሰሚና ተከታዮች ለማስደሰት ሲል፥ የሚቆጡ እንዳይቆጡ፥ እንዳያዝኑ ሲል እውነትን የሚሰቅል ሰው ነው። ይህ ሰው ከእርሱ በፊት የነበሩና ዛሬም ያሉ የቃል-እምነት ሰባኪዎች አንድ አፍ ነው። እነዚህ ሰባኪዎች ቃል የሚሉት የተጻፈውን ቃል ሳይሆን ሬማ የሚሉትን እግዚአብሔር ላንተ የሰጠህን ቃል ነው። እንደነዚህ ሰዎች አባባል ያ ላንተ የተሰጠው 'ቃል' ቀድሞ ከተሰጠው የተጻፈው ቃል ጋር ቢጻረር እንኳ ዋናው የተጻፈው ሳይሆን አንተ የተቀበልከው ነው! አምነህ፥ በራእይህ አይተህ፥ በቃልህ ተናግረህ የሚሆንልህ ነው። ስለዚህም አጉልና አሰናካይ ቃል የተቀበሉ ሰዎች 'እግዚአብሔር እንዲህ አለኝ' እያሉ በስሙ የሚናገሩአቸው በግልጽ ግን ስሕተት የሆኑ ነገሮች ይታያሉ፤ ይደመጣሉ።

ስለዚህ ብልጽግናን በማያውሉበት ብልጽግና ይሰብካሉ። የሌላ ኪስ እያራቆቱ የራሳቸውን የባንክ ሂሳብ ያደልባሉ። ፈውስ በሌለበት ፈውስ ይሰብካሉ። ሰዎች ካልተፈወሱ ሬማው ስላልመጣ ነው፤ እምነት ስለሌለህ ነው፤ መቀበል ስላልቻልክ ነው ብለው ይቀባጥራሉ። በቀኑ መጨረሻም በሽተኛው በሽተኛ እንደሆነ እነርሱም 'ፈዋሾች' እንደሆኑ ዜሮ ለዜሮ ተለያይተው ጨዋታው ይደመደማል። በሌላ ጊዜ በሌላ ቦታ ተገኝተው ተመሳሳይ ትርኢት በእውነት ላይ እየተረማመዱ ያካሂዳሉ። በተለይ እነዚህ ሁለት ርእሶች፥ የገንዘብ ብልጽግናና የሥጋ ፈውስ ምድራዊ ደስታና የኑሮ ስኬትን ጨምሮ ዋና ርእሶች ናቸው። እነዚህ የስብከት ርእሶች ምድራዊና ሥጋዊ በረከቶች ብቻ በመሆናቸው በአንድ በኩል ሥጋውያን ሰዎች የሚቋምጡላቸው ናቸው። በሌላ በኩል ዋናውን የሰውን ማንነትና ክፋት፥ ምንጩንና መንስዔውን ስለማይነኩት ሰዎችን አያስከፉም። ለስሜት መጠንቀቅ ከተጨመረበት ደግሞ ከቶም ሳይገናኙ እስከፍጻሜው መተላለፍም ይኖራል።

## መደምደሚያ

በነዚህ ሦስት ክፍሎች ሦስት የጀርባ አጥንት የሌላቸውን፥ መቆም የተሳናቸውን፥ የእግዚአብሔር ላልሆነ አሳብ እንቢ ማለት ወይም ለእግዚአብሔር እሺ ማለት ያቃታቸውን፥ በአንጻሩ ደግሞ፥ የሕዝብ ፈቃድን ለማገልገል የቆረጡና የታጠቁ መሪዎችን ነበር የተመለከትነው።

ሐዋርያው ጳውሎስ ጢሞቴዎስን እንዲጸና ሲያዝዘው፥ *ሁሉን በሕይወት በሚጠብቅ በእግዚአብሔር ፊት፥ በጴንጤናዊውም በጲላጦስ ዘንድ መልካሙን መታመን በመሰከረ በክርስቶስ ኢየሱስ ፊት አዝሃለሁ* አለው፤ 1ጢሞ. 6፥13። ጌታ በጲላጦስ ዘንድ መልካሙን ምስክርነት መሰከረ። ጲላጦስ ግን በእውነት ፊት ቀርቦ፥ እውነትን የማወቅ ድንቅ ጸጋ ገጥሞት ሳለ እውነትን ሰቀለ። የሕዝብ ሰዎች መልካሙን መታመን አለመመስከር ብቻ ሳይሆን ዛሬም እውነትንም ይሰቅላሉ፤ ይገድላሉ፤ ይቀብራሉ። በፈንታው 'በርባንን' ይፈታሉ። ሁከት ፈጣሪውን፥ ነፍስ አጥፊውን።

የሰዎች ያይደለ የእግዚአብሔር ሰው እንድንሆን ለበጎም ሥራ የቆምን እንድንሆን የጌታ ጸጋ ይብዛልን። የመንፈስ ቅዱስ እና የቃሉ ሙላት ይሁንልን። *የእግዚአብሔር ሰው ፍጹምና ለበጎ ሥራ ሁሉ የተዘጋጀ ይሆን ዘንድ፥ የእግዚአብሔር መንፈስ ያለበት መጽሐፍ ሁሉ ለትምህርትና ለተግሣጽ ልብንም ለማቅናት በጽድቅም ላለው ምክር ደግሞ ይጠቅማል*፤ 2ጢሞ. 3፥16-17።

ጌታ ከአርያም ይባርካችሁ። አሜን።

* * * * *

ዘላለም መንግሥቱ © 2011 (፪ሺህ፬) ዕዝራ ስነ ጽሑፍ አገልግሎት

# ብሮ ሠይሞ ብሞት

ወደ፡ፊትም፡ደግሞ፡ደስ፡ይለኛል፤ ይህ፡ ፲፱፤
በጸሎታችሁና፡በኢየሱስ፡ክርስቶስ፡መንፈስ፡
መሰጠት፡ስመኔ፡እንዲሆንልኝ፡አውቃለ
ሁና÷ ይህ፡ናፍቆቴ፡ተስፋዬም፡ነውና፤ በአ ፳፤
ንድ፡ነገር፡እንኳ፡አላፍርም፡ነገር፡ግን፡በሕ
ይወት፡ብኖር፡ወይም፡ብሞት÷ክርስቶስ፡ሙግ
ልዋነት፡ሁሉ፡እንደ፡ወትሮው፡አሁን፡ደግሞ፡
በሥጋዬ፡ይከብራል። ለእኔ፡ሕይወት፡ክርስ ፳፩፤
ቶስ፡ሞትም፡ጥቅም፡ነውና። ነገር፡ግን፡ ፳፪፤
በሥጋ፡መኖር፡ለእኔ፡የሥራ፡ፍሬ፡ቢሆን÷
ምን፡እንድመርጥ፡እላለታውቅም። በእነዚ ፳፫፤
ህም፡በሁለቱ፡እጨነቃለሁ፤ ልሄድ፡ክክርስ
ቶስም፡ጋር፡ልኖር፡እናፍቃለሁ÷ክሁሉ፡
ይልቅ፡እጅግ፡የሚሻል፡ነውና፤ ነገር፡ግን፡ ፳፬፤
በሥጋ፡መኖሬ፡ለለ፡እናንተ፡እጅግ፡የሚያስ
ፈልግ፡ነው። ይህንም፡ተረድቼ÷በእናንተ፡ ፳፭፡፳፮፤
ዘንድ፡አንደ፡ገና፡ስለ፡መሆኔ÷በእኔ፡መመ
ኪታችሁ፡በክርስቶስ፡ኢየሱስ፡ይበዛ፡ዘንድ÷
በእምነት፡ታድጉና፡ደስ፡ይላችሁ፡ዘንድ፡እን
ደኖር፡ከሁላችሁም፡ጋር፡እንድቈይ፡አው
ቃለሁ።

ፊል. 1፥19-26

ባለፈው የፊልጵስዩስ ጥናት የወንጌል መስፋት የደስታው ምክንያት መሆኑን አይተን ነበር። ይህ ክፍል ከዚያ የደስታ መፍሰስ የቀጠለ ነው። ቀጣይ ደስታው ከወንጌል ስብከትና ስፋት ያለፈም ነው። አሁን የራሱን መዳን ፍጹምነት እያሰበም፥ ለነዚህ ሰዎች ያለውን አገልግሎት እያሰበም ይደሰታል። ክርስትና ደስታ ነው። ወደ ኋላ አይተን ስለመዳናችን፥ ባለንበት ሁኔታም ከጌታ ጋር በመገኘታችን፥ ወደፊትም ወደ አባቱ ደስታ የምንገባ በመሆናችን እንደሰታለን።

ቁጥር 19፤ *ወደ ፊትም ደግሞ ደስ ይለኛል፤ ይህ በጸሎታችሁና በኢየሱስ ክርስቶስ መንፈስ መሰጠት ለመዳኔ እንዲሆንልኝ አውቃለሁና፥ ይህ ናፍቆቴ ተስፋዬም ነውና፤ በአንድ ነገር እንኳ አላፍርም ነገር ግን በሕይወት ብኖር ወይም ብሞት፥ ክርስቶስ በግልጥነት ሁሉ እንደ ወትሮው አሁን ደግሞ በሥጋዬ ይከብራል።*

ለመዳኔ ሲል አልዳነም ነበር ወይም ደኅንነቱ ገና የተረጋገጠ አልነበረም ማለት አይደለም። ከእስር ቤት ስለመፈታቱም መናገሩ አይደለም። ከእስር ስለመፈታት አለመሆኑን ቃሉን ቀጥለን ስናነብብም እንረዳለን። ስለሞቱ እየተናገረ ስለመፈታት ሊናገር አይችልም። እርግጥ እንደሚፈታ ተስፋ ያደርጋል፤ (ቁ. 25 እና 2፥24)። እንኳን ያለ ወንጀል የታሰረ የጌታ እስረኛ ወንጀል የፈጸመውም ለመፈታት ተስፋ ቢያደርግ ማስገረም የለበትም። ቃሉ ግን σωτηρίαν (ሶቴሪያን) ከከፉ መጠበቅንና ነጻ መሆንንም ጭምር ቢያመለክትም ዋና አሳቡ ድነት ወይም መዳን ነው። ቃሉ በክርስቶስ ያገኘነው መዳን የተገለጠበት ዋናው ቃል ነው። ክርስቶስ መድኃኒት ወይም አዳኝ ሲሰኝም ይኸው ቃል (ሶቴር) ነው የተጻፈው፤ ጳውሎስም ራሱ ይህን ቃል በ3፥20 ጽፎታል። ስለዚህ ሐዋርያው ከእስር ስለመውጣቱ መዳን መናገሩ አይደለም።

በዚሁ ምዕራፍ ቁጥር 6ን ስናጠና ጌታ ጀማሪም ፈጻሚም አምላክ መሆኑን አስተውለን ነበር። ይህ የተጀመረ ሥራም የደህንነታችን ጉዳይ መሆኑን አይተናል። በፊል. 2፥12ም ይህንን መዳንን የመፈጸም ቃል ይናገራል። ይህ መዳን መጠበቅ፥ መፈጸም፥ መጨረስ፥ ፍጹም መደረግ ያለበት ነገር ነው። ይህ የጳውሎስ መዳን እንግዲህ የመዳን መቀጠል ወይም በደኅንነት ውስጥ ሆኖ የመኖር ሁኔታ ነው። በቅድስና የማደግንን፥ በመከራ የመጽናትን፥ የሰማዩን የመናፈቅን፥ ባሉበት ቦታና ሁኔታ ለእርሱ ክብር መኖርን፥ በዚህም ሁሉ ያ ሰው የዳነ ሰው መሆኑን አመልካች ነው። ጳውሎስ መታሰሩና በመታሰሩም ምክንያት በገዛ ሕይወቱም ሆነ በወንጌል መስፋት ምክንያት በሌሎች ሰዎች ሕይወት ውስጥ የሆኑት ነገሮች የመዳኑ መገለጫዎች ናቸው።

እነዚህ ነገሮች እንዴት ወይም በምን ኃይል እንደሚሆኑ ሲናገር፥ *በጸሎታችሁና በኢየሱስ ክርስቶስ መንፈስ መሰጠት* አለ። መዳናችንን በፍሬያማነት ቀጣይ ለማድረግ እነዚህ ሁለት እጅግ አስፈላጊ ነገሮች ናቸው። የቅዱሳን ጸሎት በመንፈሳዊ ጉዞአችንና በአገልግሎታችን ብርታትና ልቀት ውስጥ ሁነኛ ሚና አለው። የኛም ጸሎት በሌሎቹ ሕይወት ውስጥ የሚሠራው ድንቅ ሥራ አለው። ሌሎች እንዲጸልዩልን መጠየቅን፥ እኛም ለሌሎች ቅዱሳን መጸለይን አናቋርጥ።

ሌላው ቃል ἐπιχορηγίας (ኤፒኮሬጊያስ) የሚል ነው። መደገፍንም መስጠትንም የሚገልጥ ἐπιχορηγέω ከሚል ቃል የመነጨ ነው። መስጠትን ሲገልጥ፥ መስፈር፥ ማቅረብ፥ መሙላት ማለት ነው። መደገፍም ማቆም፥ ማበርታት፥ እንዳይንገዳገዱ እንዳይወድቁ መያዝ ነው። ይህን የሚያደርግ ደግሞ የኢየሱስ መንፈስ ነውና ይህን መንፈስ ታመነ። የኢየሱስ መንፈስ ከመንፈስ ቅዱስ ስሞች አንዱ ነው። የፊልጵስዩስን መልእክት መግቢያ ከሐዋ. 16 ስንመለከት በተለይ ቁጥር 6-7 ላይ ይህንን አይተን ነበር። የኢየሱስ መንፈስ የሚለው ቃል በዚያ እና እዚህም ይገኛል። የሚናገረው ስለ መንፈስ ቅዱስ ሆኖ ሰጪው ኢየሱስ መሆኑን መግለጡ ነው። እግዚአብሔር መንፈሱን ሰፍሮ፥ ለክቶ፥ ቆጥቦ አይሰጥም (ዮሐ. 3፥34)። ክርስቲያን በመንፈስ ቅዱስ ቁጥጥር ወይም ሙላት ስር ሆኖ መኖር ሁሌም የሚጠበቅበት ኑሮ ነው። በክርስቲያን ሕይወት ውስጥ የመንፈስ ቅዱስ ሙላት የአንድ ቀን ክስተት ሳይሆን የየእለቱ የራስ ድካም በእርሱ ብርታትና ሁሉን ቻይነት፥ የራስ አለማወቅ በእርሱ ሁሉን አዋቂነት የሚፈጸምበት ሕይወት ነው። የመንፈስ ቅዱስ መሰጠትና ሙላት ሕይወት ነው፤ ኑሮ ነው፤ የክርስቶስ በኛ ውስጥ መኖር፤ የኛም ለክርስቶስ መኖር ነው። የመዳናችን መዳን እንደሆነ የማለቁ፥ የመፈጸሙ አካሄድ ነው።

ጳውሎስ እነዚህን ሁለት ትልልቅ ነገሮች፥ የቅዱሳንን ምልጃ እና የክርስቶስን መንፈስ መሰጠት መናፈቁ በመከራውና በእስራቱም ውስጥ ለክርስቶስ ለመኖርና እስከ ፍጻሜውም ለመጽናት የቆረጠ የቁርጥ ሰው መሆኑን አመልካች ነው። ይህ ናፍቆቱም ተስፋውም ነው። *ይህ ናፍቆቴ ተስፋዬም ነውና* አለ። ናፍቆትና ተስፋ የተለያዩ ግን ተቀራራቢ ነገሮች ናቸው። ናፍቆት ምኞት ነው፤ ሊፈጸምም ላይፈጸምም ይችላል። ግን

የውስጣችን መሻት ነው። ተስፋ ግን የሚፈጸምና በተስፋ ሰጪው ላይ የሚደገፍ ቃል ነው። ተስፋ ሰጪው የታመነ ከሆነ ተስፋው ይፈጸማል፤ ካልሆነ ደግሞ ይቀራል። ጳውሎስ በታሰረበት ወኅኒ ውስጥ ይሁን ወይም ተፈትቶ፥ በሕይወት ይኑር ወይም ሞቶ ግቡ አንድ ነው፤ እርሱም የክርስቶስ ክብር። *በአንድ ነገር እንኳ አላፍርም ነገር ግን በሕይወት ብኖር ወይም ብሞት፥ ክርስቶስ በግልጥነት ሁሉ እንደ ወትሮው አሁን ደግሞ በሥጋዬ ይከብራል* አለ።

ስለዚህ ለጳውሎስ መኖርም መሞትም ክርስቶስ እስከከበረ ድረስ ትልቅ ልዩነት የላቸውም። እንዴት ድንቅ ነው! ክርስቲያኖች የምንኖርለት ብቻ ሳይሆን የምንሞትለትም ምክንያት ያለን ሰዎች ልንሆን ነው የተጠራነው። ለምንኖርለት ዓላማ ለመሞትም ካልቆረጥን ልንኖርለት አንችልም። ይህ እውነት ነው። ለምን ቢባል ቁርጠኞች ካልሆንን እምነታችን የተግባር ሳይሆን የአፍ ብቻ ነው ማለት ነው። ለምንኖርለት ነገር ልንሞት ከተጠየቅን አንሞትማ! እንሸሻለና! ስለዚህ መኖራችን የለበጣ ነው።

ስለ ሚሊሻ በድሉ ልንገራችሁ። ያኔ የኢትዮ-ሱማሌ ጦርነት ጊዜ አንድ በድሉ የተባለ ሚሊሻ ወታደር ነበረ አሉ። አንድ ቀን የብርጌዱ አዛዥ የሆኑት ኮሎኔል፥ "እነዚህን ሽርጣም ሱማሌዎች ማየት እንዳስጠላኝ ያለ ሌላ የሚያስጠላኝ ነገር የለም። ዛሬ ያንን ኮረብታ ሄደን መያዝና እዚያ የመሸጉትን ሽርጣሞች ጨርሰን መደምሰስ አለብን፤ እሺ ጎበዝ?" አሉ። ሁሉም፥ አብዮታዊት እናት አገር ወይም ሞት! ሞት! ሁሉም ነገር ለአብዮቱ! . . . አሉና አንዳንዶቹም ፎከሩና ዘመቻው ተጀመረ። ሚሊሻ በድሉ አፈግፍጎ ወደ ሰፈር ሲሸሽ ተያዘና ማታ ኮሎኔሉ ዘንድ ቀረበ። ይህ የወታደሩን ወኔ የሚሰልብ ድርጊት በመሆኑ አዛዡ በቁጣ፥ "እህ ሚሊሻ በድሉ፥ ለምን ሸሸህ?" አሉት። ሚሊሻ በድሉም፥ "ጌታዬ ኮረኔል፥ እኔም እንደርስዎ እነዚህን ሽርጣም ሱማሌዎች ማየት እንዳስጠላኝ ያለ ሌላ የሚያስጠላኝ ነገር የለም፤ ገና ከሩቅ ሳያቸው አስጠሉኝና ጥያቸው ወደ ሰፈር መጣሁ" አለ።

ሚሊሻ በድሉ ይቅርታ ተደረገለትና ከሠራዊቱ ጋር ቆየ። በሌላ ቀን ኮሎኔሉ አቅርቦ በሚያሳይ በመነጽራቸው አንድ ጉብታ ላይ አራት ቃኚ ሱማሌዎች ያያሉ። ከወታደሮቻቸው አራቱን ይመርጣሉ። ሦስቱ ደፋሮች ናቸው፤ አንዱ ጉብዝናው መፈተሽ ያለበት ሚሊሻ በድሉ ሆነ። ኮሎኔሉ አራቱን ወደፊት ጠርተው፥ "እዚያ ጉብታ ላይ አራት ሱማሌዎች አሉ፤ እናንተ አራታችሁ ዛሬ አብዮታዊ ወኔያችሁን የምታስመሰክሩበት ቀን ነው፤ እናንተም አራት፤ እነሱም አራት፤ በሉ ግደሉና መሳሪያቸውን ይዛችሁ ኑ!" ብለው ሲያሰናብቷቸው አንዱ ወታደር፥ "ኮሮሌር፥ ኢኔ ሁላት ጋዲሎ ሁላት ማሳራ ዬዞ ዬማላሳል!" አለ። ይሽኔ ሚሊሻ በድሉ፥ "ነሽ የኔ ጅግና! እንዲያው እናት አንተን ደጋግማ መንታ አድርጋ ትውለድ! በቃ!" ብሎ አጨበጨበለትና ወደ ኮሎኔሉ ዞሮ፥ "ኮረኔል የኔን ፋንታ ደበላ ስለሚገልልኝ እኔ ቀርቻለሁ፤ ሁለተኛውን ሽርጣም የሚገድልበት ሌላ መሳሪያ ከፈለገም ይሽው የኔን ክላሽ እሰጠዋለሁ" አለ። ሚሊሻ በድሉ በሞት ቀበሌ የሚኖር ሞትን አጥብቆ የሚፈራ ሰው ነው። ጳውሎስ ከሞት ጋር ሳይፈራ የተጋፈጠ ሰው ነው።

21፤ *ለእኔ ሕይወት ክርስቶስ፥ ሞትም ጥቅም ነውና።*

ለጳውሎስ የኑሮና የአገልግሎቱ፥ የጥሪና የተልእኮው መለኪያ የክርስቶስ ክብር ነው። ስለዚህ ሞትም ሕይወትም ልዩነት የላቸውም። ለእርሱ ሕይወት ክርስቶስ ነው፤ የሚኖረው ለክርስቶስ ነው፤ የሚሞተውም በክርስቶስ ውስጥ ሆኖ ነው። የጳውሎስ ሕይወት የሚያጠነጥንበት አንድ እንዝርት፥ የሚሸከረከርበት አንድ ዛቢያ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። ሕይወት ለእርሱ ክርስቶስ ነው። ከእርሱ ውጪ ሕይወት የለም። ለጳውሎስ መኖር ማለት ክርስቶስ ነበረ። ለብዙዎች ምናልባት ሕይወት ዝናና ሥልጣን፥ ክብርና ሞገስ፥ ድሎትና ምቾት፥ አዱኛና ንዋይ፥ ሌሎችም ሊሆኑ ይችላሉ። ለእኛስ?

ጳውሎስ ሞትንም ጥቅም ነው አለ። ሞትን ጥቅም ነው ማለት የሚችል በሞት ላይ ሥልጣን ያለውን ጌታ ያወቀ ሰው ብቻ ነው። ሞት ለክርስቲያን የሚያስፈራ የንግግር ርእስ አይደለም። አንድ ጊዜ ብቻ የተወለደ ሰው ሁለቴ ይሞታል፤ በሥጋም በዘላለማዊ ሞትም። ዳግም የተወለደ ሰው ግን አንድ ጊዜ ብቻ ነው የሚሞተው። ክርስቲያን ሞትን የማይፈራው የሞት መውጊያ የተወሰደለት በመሆኑ ነው፤ 1ቆሮ. በሙሉ፥ በተለይም 15፥20 እና 55-56። ጳውሎስ ከታሰረበት ተፈትቶ ቢለቀቅ ወይም ተጠርቶ ቢገደል ለሁለቱም ዝግጁ ነው። ተርፎ ቢያገለግል ፍሬው ይበዛል፤ ሞት ተፈርዶበት ከዚህች ምድር ቢሰናበት ወደ ተሻለው ስፍራ ይሄዳል። በዚያ ስቃይም፥ መከራም፥ እስራትም፥ ግርፋትም፥ በተለይም ኃጢአትም፥ ሰይጣንም የሉም። ለጳውሎስ ሞት ጥቅም ነበረ። ለእኛስ?

22-26፤ *ነገር ግን በሰጋ መኖር ለእኔ የሥራ ፍሬ ቢሆን፥ ምን እንድመርጥ ላላስታውቅም። በእነዚህም በሁለቱ እጨነቃለሁ፤ ልሄድ ከክርስቶስም ጋር ልኖር እናፍቃለሁ፥ ከሁሉ ይልቅ እጅግ የሚሻል ነውና፤ ነገር ግን በሥጋ መኖሬ ስለ እናንተ እጅግ የሚያስፈልግ ነው። ይህንንም ተረድቼ፥ በእናንተ ዘንድ እንደ ገና ስለ መሆኔ፥ በእኔ መመካታችሁ በክርስቶስ ኢየሱስ ይበዛ ዘንድ፥ በእምነት ታድጉና ደስ ይላችሁ ዘንድ እንድኖር ከሁላችሁም ጋር እንድቈይ አውቃለሁ።*

ይህ ማለት ለመኖር ወይም ለመሞት ጳውሎስ የምርጫ ነጻነት አለው ማለት አይደለም። ይህ የእግዚአብሔር ፈቃድ እንጂ የሰው ምርጫ አይደለም። ይልቅስ ጳውሎስ እኛ ልቡን እንድናነብበና እንድናውቅ ከፍቶ እያሳየን ያለ ነው የሚመስለው። ለማንም አገልጋይ፥ በተለይም እንደ ጳውሎስ ላለ ራሱን ሳይቆጥብ፥ ለሰውነቱ ሳይሳሳ ለሚያገለግል ሰው በሕይወት መቆየት በረከት ነው። ጌታ ይከብራል፤ ነፍሳት ይድናሉ፤ ቤተ ክርስቲያንም ትታነጻለች። ለጳውሎስ መሞትም መኖርም ሁለቱም ትርጉም አላቸው። ሁለቱም እኩል ናቸው። ሁለቱም መፈታት ናቸው። እንዲያው በሥጋ መፈታትን የሰፋና የነጻነት አገልግሎት አድርገን ከቆጠርነው እንጂ ታሥሮም እያገለገለ ነው ይህን የጻፈው። ስለዚህ ሁለቱም ለእርሱ መፈታት ናቸው። ይህ ልሄድ ከክርስቶስም ጋር ልኖር የሚለው መሄድ (ἀναλῦσαι አናሉሳይ) መፈታት፥ መለቀቅ እንደማለትም ነው። እርግጥም ወደ ጌታ መሄድ መለቀቅ ነው። ወደ ጌታ መሄድ ልክ ሥጋ ከወኅኒ እንደሚወጣው መፈታት ብቻ ሳይሆን ከዚያም በላይ መለቀቅ ነው።

ጳውሎስ ቢኖር ለምን እንደሚኖር ጠንቅቆ የተረዳ ሰው ነው። ሞትም ምን መሆኑን ፈጽሞ ያወቀ ሰው ነው። መኖሩ፥ መፈታቱና ማገልገሉ ለቅዱሳን በጣም አስፈላጊ ነው። መሞቱም ጥቅሙ ነው። በሁለቱም ጌታን ማክበርን ሊያከብርበት ሁሌም ስንዱ ሆኖ የኖረ ሰው ነው። ለሚሞትለት ዓላማ የኖረ፤ ለኖረለት ዓላማም ሊሞት ቆርጦና ዝግጁ ሆኖ የኖረ አገልጋይ ነው። እኛስ እንዴት ነን? ለምንኖርለት ለመሞት፥ ለምንሞትለትም ለመኖር የቆረጥን ነን? እንድንሆን ጌታ ይርዳን። አሜን።

* * * * *

ዘላለም መንግሥቱ © 2011 (ፈሺህ፬) ዕዝራ ሰነ ጽሑፍ አገልግሎት

# የኤድስ ፈዋሽ

ይህ ጽሑፍ እንዳለፈው ስርጭት መጽሐፍ ቅዱስና የአፈታት ስሕተቶች ከሚለው መጽሐፌ ገጽ 240-247 የተወሰደ የምዕራፍ ከፍል ነው። ከመጽሐፉ በቀጥታ የተገለበጠ በመሆኑ ስለ ቅርጹ ግርድፍነት ይቅርታ እጠይቃለሁ። ጌታ ይባርካችሁ።

በመንፈስ ቅዱስና ካሪዝማዊ ቀውሶች መጽሐፍ ላይ በተጠቀሰው በመቱ የተደረገ የፈውስ ጉባኤ ላይ ልትፈወስ ሄዳና 'ተፈወስኩ' ብላ እመድረክ ላይ ስለሞተችውና ፈሳዋ ስለወጣው ሴት ተወስቶአል። በዚያው ቤቲቱ የሞተችበት ጉባኤ ላይ የተነገረ ሌላ ፈውስም ነበረ። የኤድስ ፈውስ። በዚያ የነበረ አንድ ወጣት የኤድስ በሽታ እንዳለበትና እንደተፈወሰ ያው በዚያ የተጠቀሰ ፈውሰኛ ተናገረ። የከተማዋ ሕዝብ እስኪሰሙት ድረስ ይህ የፈውስ ዜና ተስተጋባ። እጎቱም፥ የሰው አፍ የገባው ወንድሜን ጌታ ጎበኘው እያለች ብዙ የምስጋና ምስክርነት ቃል ተናገረች። በማግስቱ በነበረው ቀጣይ የፈውስ ጉባኤ ላይ የተፈወሰው ወጣት እንዲመሰክር ጊዜ ተይዞለት ነበር። ቢጠበቅ የለም፣ ሲፈለግም በአምቡላንስ ወደ ሆስፒታል መወሰዱ ተሰማ። ከጥቂት ቀናት በኋላ ከሆስፒታል ወጣ። ድኖ ሳይሆን በዚያው ሕመም ሞቶ ነበር የወጣው። ሌሎችም ጥቂት ያልሆኑ በኤድስ የተያዙ የነበሩና እንደተፈወሱ በግልም በአደባባይም እየተነገረ ግን የሞቱ ሰዎችን አውቃለሁ።

እግዚአብሔር ፈዋሽ አምላክ ነውና ሰዎችን ከምንም ዓይነት በሽታና መቅሰፍት ሊያድን እንደሚችል ፈጽሞ መጠርጠር የለብንም። እግዚአብሔር ሊፈውስ ይቻለዋል፣ ግን የውሸት ፈውሶችን እንደ እውነት መቀበል በክርስቶስ ከማመናችን ጋር አብሮ የተሰጠን ገጸታ አይደለም። ከኤድስ የተፈወሱ ሰዎችን እንደተፈወሱ ከመቀበል ብቻ ባሻገር ማረጋገጥ አስፈላጊና እንደ ዘበት ሊታለፍ የማይገባው እውነት ነው። ከኤድስ እንደተፈወሰች ከተነገራት አዘውትሬ ከምሄድባት ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ካለች አንዲት ልጅ የፈውስ ማረጋገጫ ለማግኘት ሞክሬ ነበር። ያገኘሁት መልስ ግን ይህንን ማረጋገጫ ለማግኘት አሳቡን ራሱን ማስተናገድ ተመልሶ በበሽታው ጭንቀት ራስን እንደማጠላለፍ ብቻ ሳይሆን እንደ አለማመንም እንደሚቆጠር ነበር። መጠየቁም እምነትን እንደመንደል እንደሚያስቆጥርም ነው የተነገረኝ።

ተአምራት በሚል ርእስ በፓስተር ሰይፉ ከበደ የተጻፈ መጽሐፍ ውስጥ ጸሐፊው ካያቸው ተአምራት ዝርዝር ውስጥ የኤድስ መመታትም ይገኝበታል። የእግዚአብሔርን ፈዋሽነት ባልጠራጠርም የሰማኋቸውና የገጠሙኝ የኤድስ ፈውሶች ሁሉ ውሸት ሆነው ስላገኘሁ ተጨባጭ መልስ ለማግኘትና ቃለ መጠይቅ ለማድረግ ከኤድስ የተፈወሱ ሰዎችን ስምና አድራሻ ከደራሲው ጠይቄ ነበር። እስከዚህ ጽሑፍ ሕትመት ድረስ መልስ አላገኘሁም።

በናሙና ኮንፈረንስ ምዕራፍ የተጠቀሰው ሰባኪ አሁን ከምናርበት ስፍራ ባልራቁ ሁለት የኢትዮጵያውያን ቤተ ክርስቲያኖች ውስጥ ከኤድስ የተፈወሱ ሰዎች መኖራቸውን በዚያው ጉባኤ ላይ ሰብኮ ነበር። ይህን ለማረጋገጥ ከመጋቢዎቹ ማረጋገጫ ላገኝ ሞክርኩ። እነዚህ ሁለት አብያተ ክርስቲያናት ያሉአቸው ምዕመናን ጥቂት ስለሆኑ እንዲህ ያለ ነገር ቢከሰት በመጋቢዎቹና በምዕመናኑ ቀርቶ እውቂ ባሉትም በብዙዎች ይታወቃል። ግን ከኤድስ እንደተፈወሱ ማረጋገጫ የሚያስጨብጡ በሽተኞች በሁለቱም አብያተ ክርስቲያናት አልነበሩም። ለምሳሌ፥ ከሁለቱ የአንደኛዋ ቤተ ክርስቲያን መጋቢ እንዲያ ያለ ሰው መኖሩን ስጠይቀው "አዎን" አለኝ። እርግጠኛ ፈውስም እንደሆነ ነገረኝ። ያ ሰው ስለመፈወሱ በሐኪም የተረጋገጠ ወረቀት እንዳለው ጠየቅኩት። እንደሌለው ነገረኝ። ቀድሞ የኤድስ በሽተኛ ለመሆኑስ ማረጋገጫ እንዳለው ስጠይቅ አሁንም እንደሌለው ነገረኝ። እንግዲህ ይህ ሰው በኤድስ የተያዘም ሆነ የተፈወሰ ስለመሆኑ ማረጋገጫ የለም። ይህንን ነገር ለማረጋገጥና እውነትነቱን ለማጣራት እንደምፈልግ ነግሬ ከሰውየው ጋር ለመገናኘት እንዲረዳኝ ጠየቅኩት። ለዚህ ጥያቄ የተሰጠኝ መልስ ጠንካራ "አይቻልም" ነበር። ለምን እንደማልችል የነገረኝም የይሉኝታ ችግር፥ የባህላችን ምስጢር የመደበቅ ነገር፥ እንዲሁም ሰውየው በኤድስ መያዙን ሰዎች ካወቁበት ምን ይሉኛል ባይነቱ ነበር። መጋቢው ግን ፈውሱን ያምናል። እንዴት እንዳመነ ስጠይቀው በሽተኛው በግል ካጫወተው በመነሣት ሲመረመር የኤች አይ ቪ ካውንቱ ወይም በደም ሴሎች ውስጥ የሚቆጠረው የቫይረስ መጠን እንደቀነሰ በመናገሩ ነው። ይህ 'ካውንት' የሚባለው ደም ወስደው ሲመረምሩ በደም ውስጥ ያለው የቫይረሶቹ ቁጥር ሲጨምርና ሲቀንስ የሚሆነው ነገር ነው። ይህ ቁጥር እንዳንደ ይጨምራል፣ ሌላ ጊዜ ደግሞ ይቀንሳል። እንግዲህ ያ ሰው ተፈወሰ ከተባለ በኋላ በእንዱ ምርመራ ወቅት የቫይረሱ ካውንት ቀነሰ እንጂ እንዳለተፈወሰ ግልጽ ነው። ይህ ሰው ቀድሞም ኤድስ እንዳለበት ሳይታወቅ፥ ኋላም ተፈወሰ ተብሎ በጉባኤው ውስጥ ይገኛል።

እግዚአብሔር ፈዋሽ ነውና ቢፈውስ መደነቅ አለበት። የዚያኑ ያህል ደግሞ ያልተፈወሱትን እንደተፈወሱ የሚናገሩ ፈውሰኞች ስሕተታቸው ሊነገራቸው ይገባል። ችግሩ የፈውስ ስጦታ አለን ባዮቹ ብቻ አይደለም። ከበሽተኞችም ሳይፈወሱ የተፈወሱ እየመሰላቸው የተሞኙ ጥቂት አይደሉም። አንዳንዶች በየዋኅኑ ከኤድስ መፈወሳችሁን ተቀበሉ ስለተባሉ ጉም እየዘገኑ ሳይመረመሩ የትዳር ጓደኛ ፈልገው ኢያገቡ ለሌላ ጠንቅ የሆኑ አሉ። አንዳንዶቹ ከልባቸው ያለመፈወሳቸውን እያወቁ ግን እንደተፈወሱ ሆነው ቀድሞ ያጡትን ተቀባይነት አግኝተው እየተደሰቱበት መጠቀሚያ ያደረጉትም አሉ። እንዲህ ያለ አንድ ደፋር ሰው አይቻለሁ። ደፋር ያልኩት በየዋኅኑ ተፈውሻለሁ ብሎ የሚወዛወዝ ሳይሆን ሊያድበረብርበት የሚሞክር መሆኑን በማረጋገጥም ነው።

የዚህ ሰው 'ፈውስ' ታሪክ እንዲህ ነው። በ89 ዓመተ ምሕረት ታኅሣሥ 13 ቀን በአዲስ አበባ ባለች አንዲት የቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን የአምልኮ ጊዜ አንድ ሰው ከኤድስ እንደተፈወሰ መሰከረ። እንዲፈወስ የጸለየለት ሰው በዕለቱ ይሰብክ ነበርና ከስብከቱ ጊዜ ቆርሶ ለተፈወሰው ሰው በሰጠው የምስክርነት ዕድል ነው ምስክርነቱ የተደመጠው። ሰውየው እንዴት በመሰለ አስደናቂ ሁኔታ ጌታ እንደፈወሰው መሰከረ። ጉባኤውም በተሰመደ የተጋነነ ሆታና እልልታ ቤቱንም ዳሱንም ሞላው። በጊዜው በቃለ ሕይወት ሥነ ጽሑፍ አገልግሎት ውስጥ እሠራ ነበርና የፈውሱን ዜና ሰማሁ። ይህ ከሆነበት ቀጥሎ ባለው ሳምንት አጋማሽ ላይ ከሥራ ባልደረባዬ ጋር በመሆን በዚያችው በተፈወሰበት ቤተ ክርስቲያን ለዚሁ ሰው ቀጠሮ ተይዞ ቃለ መጠይቅ አደረግንለት። ከሕመሙ እንዲፈወስ የጸለየለትንም ሰው አነጋግረን ነበር። ሁለቱንም ያነጋገርነው እግዚአብሔር ፈዋሽ አምላክ ነውና ይህ ነገር እውነት ከሆነ የእግዚአብሔር የፈውስ ሥራ አዋጅ ተብሎ እንዲነገር፣ ካልሆነም ውሸታም ፈውስ ነውና ከሐሰተኛ ፈውሰኞችና ተፈጥሮች ሰዎች እንዲጠነቀቁ ምዕመናንን ለማሳሰብ ነበር።

እንደተፈዋሹ ምስክርነት በጦር ሠራዊት ውስጥ ሲያገለግል ሳለ በበሽታው እንደተለከፈና በተጨማሪም የሳንባ በሽተኛ መሆኑንም ነገረን። የሳንባ በሽተኛ ለመሆኑ ከሳንባ ነቀርሳ ክሊኒክ የተሰጠውን መታወቂያ ለማረጋገጫ አሳይቶናል ከዚህኛው ሕመም መፈወሱን ግን አልተናገረም። በዚያው መታወቂያ ላይ የተጻፈው በሐኪም እንደሆነ የነገረን የኤድስ በሽተኛ መሆኑን የሚመሰክር የእጅ ጽሑፍም አለበት። ሰውየው ስለ ሕመሙ በሰፈው ከነገረን በኋላ ስለ ፈውሱም በሰፈው መሰከረልን። ከሦስት ሳምንታት በፊት በቤተ ክርስቲያኒቱ በሚደረገው መደበኛ የዐርብ የጸሎት ጊዜ ተገኝቶ ሳለ አገልጋዩ እጁን ጭኖ ሲጸልይለት ኃይለኛ እንደ ኮረንቲ ያለ ንዝረት እንደተሰማውና በሰውነቱ ላይ የነበረው ቁስል በማግስቱ እንደደረቀ ነገረን። ወደ ሐኪሞቹም ዘንድ ሄደ መፈወሱን እንደነገራቸውና አነርሱም እንደገና መርምረው ነጻ መሆኑን እየተገረሙ እንደነገሩት አወጋን። አስፈላጊ ማስታወሻዎችንና ምስሎችን ከወሰድን በኋላ ለሚቀጥለው ቃለ መጠይቅ ከሐኪሞቹ የተሰጠውን ከኤድስ ነጻ የመሆኑን ማረጋገጫ ወረቀት እንዲያመጣና እንዲያሳየን፥ የሐኪሞቹንም ስምና አድራሻ እንዲሰጠን ተስማምተን ቀጠሮ ይዘን ተለያየን።

በቀጣዩ ቀጠሮ በተባለው ሰዓት ቃለ መጠይቁን ያደረግነው ሁለታችን እንዳሁም የክፍላችን አለቃና የመሥሪያ ቤታችን የሕዝብ ግንኙነት ክፍል ሠራተኛ ተያይዘን ሄድን። በቀጠሮው ጊዜና በቦታው ተገኝተን ሁለት ሰዓት ያህል ከጠበቅነው በኋላ ስላልመጣ ትተን ተመለስን። በቃለ መጠይቁ ወቅት የያዝናቸው ውሸት እንደሆኑ የተረዳናቸው ነጥቦች ነበሩ። በዚያው ቀን ስለ እርሱ ሌላ አስደንጋጭ ነገር ሰማንና ያንንም ለማስረገጥ በሳምንቱ ውስጥ አስፈልገን ልናገኘው አልተሳካልንም። የዚህኛውን እውነትነት ለማረጋገጥ ግን ከሚያውቁት ሦስት የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች ጋር ባደረግነው ቃለ መጠይቅ ይህ ሰው ከዚያ ጊዜ ሁለት ዓመታት በፊት በቀጠና ሁለት ሙሉ ወንጌል ቤተ ክርስቲያን ከኤድስ ተፈወሰ የተባለለትና እርሱም ተፈወስኩ ብሎ ሰፊ አድና ቆትን ያተረፈ፥ በአንድ ክርስቲያናዊ ጋዜጣም ታሪኩ የተጻፈለትና ብዙ የዋህ ክርስቲያኖችም በተሰያዩ መንገዶች የገንዘብና ሌሎችም እርዳታ ሲያደርጉለት የቆየ ሰው መሆኑን፥ አሁን ያ እርዳታ ከወዲያ በኩል ሲመነምን ወደዚህችኛዋ ቤተ ክርስቲያን መጥቶ ተመሳሳይ ድራማ ሊሠራ እየሞከረ መሆኑን ነገሩን። ደፋሩን ሰው ከዚያ በኋላ ልናገኘው አልቻልንም። እንደፈወሰው ለመሰለው ሰው ግን ጉዳዩን ስንገልጥለት አገልጋዩ የእርሱን ጸጋ እንዳጣጣልንበት ብቻ ነበር ጉዳዩን የወሰደው እንጂ የእደጋው ግዝፈት አልታየውም። የውሸት ፈውሶችን ያለፈቃድ እያባዙ የሚሸጡ ፈውሰኞች ዝም መባል ያለባቸው እስከ መቼ ነው? ፈውሶችስ በማይረጋገጡ በሽታዎች ብቻ ላይ ተጣብቀው የሚቀሩት እስከመቼ ይሆን?

የውሸት ፈውሶች በፈዋሾችም ይደረጉ ወይም በተፈዋሾች ችግራቸው ቶሎ የሚቀረፍ አይደለም። ከፈውሱ ያለመናር አካላዊ ጉስቁልና ባሻገር ስሜታዊና መንፈሳዊ ኪሳራ አለበት፤ በማያምኑትም ዘንድ ሳይቀር የሚፈጠር የስም መጉደፍና ሞራላዊ ዝቅታ ይከተላል። ይህ ደግሞ በተራው የወንጌል ሩጫን የሚያስዘግምና ምስክርነትን የሚያጎድፍ ነው። ባለፉት ጥቂት ዓመታት በኬንያ ውስጥ እንዲህ ያሉ የውሸት ፈውሶች እጅግ እየበዙ ውሸትነታቸው በአማኞችም በዓለማውያንም ዘንድ በግልጽ እየታየ መጥቶ የቤተ ክርስቲያን መነወሪያና የእግዚአብሔር ስም መሰደቢያ ሆኖ ነበር። *The Nation* የተባለ የአገሪቱ ጋዜጣ ስለነዚህ የተለምር ፈውሰኞች እነሂህን *የታለምር ነጋይዎች ለሰወግዱልን* በሚል ርእስ አንድ መጣጥፍ ጽፎ ነበር። በውስጡ ከተጻፈው መሐል፥

> እነዚህ ዳንን የሚሉ ሰዎች እነማን ናቸው? ከየት ነው የመጡት? ለምንድነው ሁሌ እንግዳና የማይታወቁ የሚሆኑትና ከዚያ በፊት ያልታወቁ ከዚያም በኋላ የማይኙ የሚሆኑት? እንደሚታወቀው እያንዳንዷቷ የኬንያ ከተማ የሚታወቁ ዐይነ ስውር ለማኖችና አካለ ስንኩላን አሉአት። ከእነዚህ አንዳቸው ተፈውሰው ቢሆን የከተማዋ ነዋሪዎች ሁሉ ተአምር መፈጸሙን ያምኑ ነበር። ይሁን እንጂ እኒህ ታላላቅ ወንጌላውያን መጥተው ሲሄዱ ዕውርና አንካሳ ለማኖቻችንን እዚያው የነበሩበት ነው የምናገኛቸው። ይህ መጽሐፍ ቅዳሳዊው ተአምራዊ ፈውስ ልማድ ከቶም አይደለም። እነዚህ ወንጌላውያን በስሙ የሚነግዱበት ኢየሱስ ክርስቶስ ተአምራቱን ይፈጽም የነበረው በስውር አልነበረም፤ ደግሞም ሰዎች እውነትነቱን እንዲያረጋግጡት አይከለክልም ነበር። በሉቃ. 5፥12 ኢየሱስ ለምጻሙን ከፈወሰ በኋላ ሰውየው ወዲያው ሄዶ ራሱን ለካህናት እንዲያሳይና መፈወሱ እንዲረጋገጥ ነበር የሳከው።[41]

ይህ ከአማኙም ከአላማኒውም ሰፊ ተነባቢ ያለው ብሔራዊ ጋዜጣ ነው። ፈውሶቹ ሐሰተኞች ከሆኑ የሚስተጋባው አሉታዊ ተጽዕኖ ቀላል አይደለም። ወደ ኤድስ ስንመለስ ደግሞ ቀሳፊነቱና ተዛማችነቱ የፈውሱን እርግጠኝነት የሚያስጠይቅ ቢሆን ይህን ማረጋገጫ መጠየቅ የሴሎችን እምነትና ፈውስ እንደማፍረስ፥ እንዲሁም እንደ ነውር መቆጠር የለበትም። ኤድስን ሰውም ይሥራው የሰማይ ቁጣም ይሁን ከዘመናችን ክፉ መቅሰፍቶች አንዱ መሆኑ እሙን ነው። እግዚአብሔር ፈዋሽ አምላክ መሆኑን ሳንዘነጋ ኤድስን እንደ ሕመም ወይም እንደ ደዌ ካየነውና ፈውስ ተደረገ ከተባልን እነዚያ ተፈወሱ የተባሉ ሰዎች እንደዋዛ ከመደባለቃቸው በፊት ማረጋገጥና ማረጋገጫ መጠየቅ እንደ ከሃዲነት ወይም እንደ እምነት አፍራሽነት መታየቱ አግባብ አይደለም። ለዚህ ጥሩ ምሳሌ የሚሆነን ከላይ በኬንያው ጋዜጣም እንደ ምሳሌ የተጠቀሰው በሉቃ. 5፥12-14 ያለው የጌታ የፈውስ አገልግሎት ክፍል ነው። ይህን ክፍል ከመጠነኛ ማብራሪያ ጋር እንመልከተው።

> *12፥ ከከተማዎችም በአንዲቱ ሳለ፥ እነሆ፥ ለምጽ የሞላበት ሰው ነበረ፤ ኢየሱስንም አይቶ በፊቱ ወደቀና፥ ጌታ ሆይ፥ ብትወድስ፥ ልታነጻኝ ትችላለህ ብሎ ለመነው።*
>
> *13፥ እጁንም ዘርግቶ ዳሰሰውና፥ እወዳለሁ ንጻ አለው፤ ወዲያውም ለምጹ ለቀቀው።*
>
> *14፥ እርሱም ለማንም እንዳይናገር አዘዘው፥ ነገር ግን፥ ሄደህ ራስህን ለካህን አሳይ፥ ለእነርሱም ምስክር እንዲሆን ስለመንጻትህ ሙሴ እንዳዘዘ መስዋዕት አቅርብ አለው።*

ጌታ በገሊላ አካባቢ ካሉት ከተሞች በአንዲቱ ሳለ አንድ ለምጻም መጣ። እንደዛሬው ሁሉ በዚያን ዘመን እስራኤልም ሁለት ዓይነት ለምጽ ነበረ። አንደኛው የቆዳ ለምጽ ነው። የላይኛውን የቆዳ ቀለም እየበላ የሚሰፋ፥ ጥቁርና ጠይሞችን ቀይ፥ ቀዮችን ደግሞ ነጭ የሚያደርግ የቆዳ በሽታ ነው።

ሁለተኛው ግን ከቆዳ አልፎ ወደ ሥጋ ውስጥ የሚገባ ከሰውነት ጫፎች በአንዱ ወይም በጥቂቱ፥ በእጅ ወይም በእግር ጣት፥ በአፍንጫ፥ በጆሮ ጫፎች ይጀምርና ወደ መሐል እየሰረሰረ የሚሄድ፥ ሥጋን ሁሉ እየበላ የሚዛመት የነርቭ በሽታ ነው። ጣቶች አልቀው የእጅ ወይም የእግር ጉቶ ብቻ እስኪቀር ድረስ የሚጎመድ፥ የሚቆምጥ በሽታ ነው። የዚህ በሽታ ዋና ክፋት ነርቮችን ስለሚገድል በሽተኛው ሕመሙ አይሰማውም። እየቆሰለ፥ እየተቆረጠ፥ እየተወጋ ምንም አይሰማውም። በሕይወት እያሉ አካል ማለቅ፥ መሞት ይጀምራል። ቁምጥና የሚባለው ይህ በሽታ ነው። በመጽሐፍ ቅዳስ ግን ሁለቱም ለምጽ ተብለው ነው የተጠሩት። ለምጽን ወይም ቁምጥናን በተመለከተ በብሉይ ኪዳን የተሰጠ ሰፊ ሕግ ይገኛል። ከድንጋጌዎቹ መካከል አንዱ ከማኅበረ ሰቡ እንዲለይ የሚያዘው ነው። በተለይ ዘሌ. 13፥45-46 ልብሱ የተቀደደ፥ ራሱ የተገለጠ፥ ከንፈሩ የተሸፈነ እንዲሆን፥ ሰው እንዳይቀርበውና እንዳይነካው ለማስጠንቀቅ፥ "ርኩስ ርኩስ ነኝ" እያለ እንዲናገር፥ መኖሪያው ከሰፈር ውጭ ሆኖ ብቻውን እንዲኖር ያስጠነቅቃል። ከጎብረተ ሰቡ ወጥቶ፥ ከቤተ ሰብ ተለይቶ፥ ተሰድዶ ለብቻው ይኖራል። የማንም ትከሻ አይገፋውም፤ የማንም እጅ አይዳስሰውም። ተጋፍቶ መኖር ትልቅ በረከት መሆኑን የሚያውቅ ሰው ነው። ይህ ለምጽ ወይም ቁምጥና ኃፍረት፥ ፍርሃትና ድንጋጤ የሞላበት በሽታ ነው። ጥንትም ዛሬም እንደሚነገረው እነዚህን በሽተኞች የሚጎዳቸው ከአካላዊው ጉዳት ይልቅ ጎሊናዊው፤ ስነ ልቡናዊው ስቃይ ነው። ሰው ሁሉ ሲያያቸው የሚዘገንነው፥ የማይቀርባቸው፥ የማይነካቸው፥ ከሩቅ የሚሸሻቸው ናቸው። ለእንደዚህ ያሉ ሰዎች ሰዎችን ከመንካትና በሰዎች ከመነካት የበለጠ ምንም የሚያስደስታቸው ነገር የለም።

እንዲህ ያለው ለምጻም ሰው ነበር ወደ ኢየሱስ የመጣው። ይህ ሰው በቆዳው ለምጽ ሳይሆን በቁምጥናው ለምጽ የተያዘ ነው። ለምጻም ሳይሆን ለምጽ የሞላበት ነው የተባለው። ይህ ሰው ሊነካው ቀርቶ ማንም የማይቀርበው ዓይነቱ ለምጻም ነው። ስለ ኢየሱስ የነበረው እውቀት ግን በቂ ነበር። 'መምህር ሆይ' ሳይሆን 'ጌታ ሆይ' ነበር ያለውና የጌታን ጌትነት ያወቀ፥ ያመነና የተተበለ ይመስላል። ይህ ሰው አንድ ሌላ ነገርም የተረዳ ይመስላል። ኢየሱስ ሊያነጻው እንደሚችል ወይም ችሎታ እንዳለው እውቆአል ግን ሊያነጻው እንደሚወድ እርግጠኛ አይመስልም። በእግዚአብሔር ዘንድ መቻልና መውደድ የተለያዩ ነገሮች ናቸው። እርሱ ሁሉን ቻይ ነው። ሁሉን ማድረግ ይችላል። የሚችለውን ሁሉ ግን ያደርጋል ወይም ሊያደርግ ይወድዳል ማለት አይደለም። ለምሳሌ፥ እግዚአብሔር መፈወስ ይችላል፤ ነገር ግን መፈወስ ይችላል ማለት ፈቃዱ ሁሉ ፈውስ ነው ማለት አይደለም። የፈቃዱን እውቀት የማወቅ አስፈላጊነት እዚህ ላይ ነው። ወደ ኢየሱስ መጣና በፊቱ ወድቆ ጌታ ሆይ ብትወድስ ልታነጻኝ ትችላለህ አለው። ጥያቄ አይደለም። ብትወድ፥ ብትፈልግ ትችላለህ ማለቱ ነው። ይህ ሰው የማይቀርበውና ወደ ሰው መቅረብ የሌለበት ሰው ነው። ሁሉ የሚጸየፉት ይህ ሰው ሰውን ሁሉ አልፎ ወደ ኢየሱስ መጣና በፊቱ ወደቀ።

እጁንም ዘርግቶ ዳሰሰውና፥ እወዳለሁ ንጻ አለው፤ ወዲያውም ለምጹ ለቀቀው። በብሉይ ሕግ ለምጻምን መንካት ርኩስን መንካት ነው። ርኩስን መንካት መርከስ ነው። አይሁድ ላለመርከስ በጣም ይጠነቀቃሉ። ጌታ ግን ነካው። ዳሰሰው። የማይነካውን ነካ! መንካት ብቻ አይደለም፤ ሰዎች ሁሉ እጃቸውን ወደሚሰበስቡበት ሰው እጁን ዘረጋና ዳሰሰው። እወዳለሁ ንጻ ብሉ ቃልን ተናገረ። ሳይነካው ቃልን ብቻ መናገሩ ሊፈውሰው ይችል ነበር። እርሱ ግን ከዚያም ያለፈ አደረገ። በጌታ ዘንድ ፍቅር ከሕግ በላይ ነው። የዳሰሰው ሕጉን ለመሻር ሳይሆን ፍቅርን ለመግለጥ ነው። ለፈውሱ ቃልን መናገሩ በቂ ቢሆንም የሰውየውን ጥልቅ የፍቅር ናፍቆት፥ የመዳሰስ ፍላጎት ግን ቃልን መናገሩ አይደርስም። ስለዚህ ይህንን ለመድረስ ዳሰሰው። ይህ ከቆዳውና ከሥጋው ያለፈ የልብ ቁስል ፈውስ ነው። እሱና ጌታ የሚያውቁት የውስጥ ፈውስ ነው። ኋላ ሄዶ ራሱን ለካህን ቢያሳይም ካህኑ የተፈወሰ ሥጋውን እንጂ የተጠገነ ልቡንና ሙሉ የሆነ እሱነቱን አያይም። ይህ ድንቅ ጌታ ነው። ይህ ድንቅ እውነት ነው። ዛሬም ያልተለወጠ ባህርዩ ነው።

እርሱም ለማንም እንዳይናገር አዘዘው፥ ነገር ግን፥ ሄደህ ራስህን ለካህን አሳይ፥ ለእነርሱም ምስክር እንዲሆን ስለመንጻትህ ሙሴ እንዳዘዘ መስዋዕት አቅርብ አለው። በመጀመሪያ ለማንም እንዳይናገር አዘዘው። ይህን ያለው ምናልባት ወሬው ያለልክ ተዛምቶ የወሬና ተአምር የሚጉ ናፍቆት ያላቸው ሰዎችን ስብሰባ ለማስቀረት ይሆን? ቀጥሎም ራሱን ለካህን እንዲያሳይና መስዋዕት እንዲያቀርብ አለው። ይህ መስዋዕት በዘሌ. 14 የተጠቀሰው ነው።

ራሱን ለካህን ማሳየቱ አስፈላጊ ነበር። ካህን በብሉይ ኪዳን የፈውስ አስረጋጭ፥ ነጻ መሆኑን የሚያረጋግጥ፥ መፈወሱን የሚያረጋግጥ፥ ወይም በዘመናዊ ቋንቋ ነጻ ነው የሚል የምስክር ወረቀት እንደሚሰጥ ሐኪም ነው። ለምጹ መጥፋቱ በሰውነቱ ይታያል። ግልጽ ነው። ማኅበረ ሰቡ ግን ሊቀበለው ይከብደዋል። አሁንም ለምጻም ይመስለዋል። ኢየሱስ በሽታውን ብቻ ሳይሆን ማኅበራዊ ግንኙነቱንም ሊፈውስ ወደ ካህን ላከው።

አንዳንድ ሰዎች ከተፈወሱ በኋላ ሄደው ሐኪም እንዲያዩ ሲነገራቸው አገር ጥለው መጥፋት ያሰኛቸዋል። ለምን ሲባሉ እምነት ማጣት ይመስላቸዋል። የፈወሱአቸው ሰዎች ስለ እምነት ረቂቅና የማይጨበጥ ትምህርት ሰጥተዋቸዋል። በመጽሐፍ ቅዳስ ውስጥ ምንም እንዲህ ያለ ነገር ባናገኝም ፈውሰኞቹ ተፈዋሾቹን ከተጠራጠሩ በሽታው እንደሚመለስባቸው ያስፈራራሉ። ስለዚህ ወደ ሐኪም ሄዶ መፈወስን ማረጋገጥ በደል መስሉአቸው ተፈውሰሃል ተብለው፥ ተፈውሻለሁ ብለው ይኖራሉ። በድንገትም ይሰናበታሉ። ምን ሆነ? ሲባል ወደ አምላኩ ተሰበሰበ ይባላል። እርግጥ በክርስቶስ ካመነ ወደ አምላኩ ተሰብስቦአል። ግን ምን ሆኖ? ለሚለው ጥያቄ ምላሽ አይሰጥም። ጥያቄው እንዲነሣም አይፈለግም። ስለዚህ ያልተፈወሱ ተፈወሱ ሲባል ጠንቃቃ እንሁን። ይህ አሳብ በቀደመው መጽሐፍ የፈውስ ቀውስ ስር ብዙ ተብሎበታል።

በጌታ የተፈጸመው ተአምር ምንም ያልጎደለው ተአምር ነው። አድራጊው ደግሞ ራሱ ጌታ ነው። ከተፈወሰ ተፈውሰሃል ብቻ ብሉ ለምን አልተወም? ለምን ሄዶ ራሱን ለካህን እንዲያሳይ አለው? ምክንያት ነበረው። ድውዩ ለራሱ ተፈውሶአል፤ ለሌላውም ፈውሱን ማረጋገጥ አለበት። ፈውስ የሆነላቸው ሰዎችም በሰውነታቸው አውቀውታል። አንዳንዱ ፈውስ ግን ዝም ብሉ ከመደባለቅ በፊት ሌላ ማረጋገጫ ይፈልጋል። ያለጥርጥር ኤድስ ከነዚህ አንዱ ነው።